# ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ያላቸው ተፈፃሚነትና ያሉ ተግዳሮቶች

**ጥናቱን ያከናወኑ ባለሙያዎች:-**

ዶ/ር መሰንበት አሰፋ

ታደለ ተካ

- ህገ መንግስታዊ ድንጋጌዎች ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን የሚይዙ በመሆናቸው በይዘታቸው ሰፊና በጥቅሉ የተቀመጡ ናቸው፡፡ ሰብአዊ መብቶች መሰረታዊ የሰው ልጆች ነጻነቶች በመሆናቸው ከሌሎች ጉዳዮች የሚለያቸውምክንያት አንዱ ጥበቃ የሚደረግላቸውም በህገ መንግስት መሆኑ ነው፡፡ የኢ.ፌድ.ሪ. ህገ መንግስት ሰፊ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችን የደነገገና ትርጉማቸውን አስመልክቶም ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸውን የሰብአዊ መብት ስምምነቶች አስመለክቶም ዝርዝር ትርጉማቸውን ለመረዳት አነዚህን የሰብአዊ መብት ስምምነቶችና የሰብአዊ መብት ሰነዶች ማየቱ ተገቢ እንደሆነ በግልጽ ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን ፍርድ ቤቶችን አስመልክቶ ያለውን ልምድና አሰራር ስናይ የተለያዩ የህግ፣ የአመለካከት የአሰራር ልምድና ሌሎች ተያያዥ ምክንያቶች የአለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች በፍርድ ቤቶች ያላቸውን አፈፃፀም ውስን አድርጎታል፡፡
- አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ያላቸውን አፈጻፀም በተገቢው ሁኔታ ለማጠናከር የህግ ጉዳዮችን አስመለክቶ ብቻ ሳይሆን መሰራት ያለበት የግንዛቤ፣ የአሰራርና የአመለካከትና እንዲሁም የሌሎች ሃላፊነት ያለባቸው ተቋማት ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም የህግ አውጭው፣ የሰብአዊ መብት ተቋማት የትምህርትና የጥናት ተቋማት ከፍተኛ ሃላፊነት አለባቸው፡፡
- የፌደራል ፍርድ ቤቶች ውሳኔዎች በተለይም የፈዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔዎች በህትመት መልክ በማቅረብና በድህረ ገፅ ለህዝቡ የማቅረብ ሁኔታ ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊታይ የሚገባው ጉዳይ ግን ፍርድ ቤቶቹ አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶችን የተጠቀሙባቸው ውሳኔዎችን ለብቻ በክፍል ወይም በምዕራፍ የሚወጡበት ሁኔታ ቢኖር በተሻለ ሁኔታ የሚታወቁበት እድል ይኖራል፡
- አለም አቀፍና ሀገራዊ ልምዶች በስፋት እነደሚያስረዱት ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶችን በፍርድ ቤቶች ለማስፈፀም የማይተናነስ የህግ ማእቀፍ እነዳላት ነው፡፡ በመሆኑም

በስፋት ሊሰራበት የሚገባው ጉዳይ ተግባራዊ ተኮር የሆነ የስልጠና ስራ ነው። በተለይም አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች በማስረዳት ዙሪያና ለዚህ በጣም ጠቃሚ የሆኑትን አጠቃላይ ትንታኔዎችና አጋዥ ሰነዶች ለዳኞች በአግባቡ ማሳወቅ ወሳኝ ነገር ነው። ይህን አስመልክቶ የተወሰነ ግንዛቤን ማስጨበጥ ስራ ቢሰራም ለዚህ ጥናት በተዘጋጀው መጠይቅ እነደሚያሳየው 28% የሚሆኑት የፌዴራል ፍርድ ቤት ዳኞች አይደለም ዝርዝር የአለም አቀፍ ሰነዶችን ይቅርና ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸውን ሰምምነቶችን እነደማውቁ ነው። ይህም ግንዛቤ በማስጨበጥ ዙሪያ ከፍተኛ ስራ መሰራት እነዳለበት ነው። በተለይም ከሰብአዊ መበት ስምምነቶች አፈጻጸም ጋር ግንኙነት ያላቸው አጠቃላይ ትንታኔዎች (General Comments) ፣ ኢትዮጵያን አስመልክተው የተሰጡ የመፍትሄ ሃሳቦችና (Concluding Observations) እና ሌሎች የማብራሪያ ሰነዶችንና ውሳኔዎችን የማስተዋወቅ ስራ ይጨምራል። እነዚህ የሰብአዊ መብት ሰነዶች ዝርዝር ጉዳዮችን ከመያዛቸውም በላይ አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶችን በ ሃገር ደረጃ ከማስፈፀም አንፃር አይነተኛሚና አንዳላቸው የሚታወቅ ነው። እነዚህ ሰነዶች አለማቀፍ የሰብአዊ መብቶችን ለማስፈፀም ትልቅ ሚና ቢኖራቸውም መብቶቹን የማስፈፀም ሃላፊነት ያለባቸው የተለያዩ የመንግስት አከላት በበቂ ሁኔታ ሊረዷቸውና ሊተገብሯቸው ይገባል።

- አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ያላቸውን አፈፃፀም በምናይበት ጊዜ ሰብአዊ መብት ስምምነቶቹን ይዘት መለየት ተገቢ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ በቀጥታ ተፈፃሚነት ያላቸውና ለፍርድ ቤቶች አሰራር የማይከብዱ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች አንዳሉ መለየት ተገቢ ነው። በመሆኑም አንዳንድ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችን የያዙ ስምምነቶች ለምሳሌ እነደ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መብቶች ለፍርድ ቤቶች አፈፃፀም አስቸጋሪ ቢሆኑም ብዞዎቹ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች ለአፈፃፀም አመቺ የሆኑና በፍርድ ቤቶች ሊተገበሩ የሚችሉ ናቸው።
- አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶችን ማፅደቅ የሰብአዊ መብት ስምምነቶችን ለማክበር እነደመነሻ

የሚወሰዱ እነጂ የመጨረሻ መሆን የለበትም፡፡ ይህ ማለትም አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች በፍርድ ቤቶች ያላቸውን ተፈፃሚነት ለማረጋገጥ ሙሉ ይዘታቸውን በነጋሪት ጋዜጣ ማውጣት አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ ለዚህ ጥናት ተብሎ በተደረገው ቃለ መጠይቅ 77% የሚሆኑት ዳኞች በግልፅ እነዳስቀመጡት የስምምነቶቹ ሙሉ ይዘታቸው በ ነጋሪት ጋዜጣ መውጣት ለአፈፀፀም በእጅጉ እነደሚረዳ አስረድተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሌሎች ሀገር ልምድ እነደሚያሳው በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ለምሳሌ የህፃናት መብት፣ የሰወች ህገ ወጥ ዝውውርና ሌሎች ሀገሪቱ ትኩረት የምትሰጣቸው ጉዳዮች ላይ ልዩና ዝርዝር አዋጆች ማውጣት ለአፈፀፀም ይረዳል፡፡

- ኢትዮጵ ያፀደቀቻቸው አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶችን አስምልከቶ በዳኞች ተለይቶ የሚገለፀው አንዱ ጉዳይ ኢትዮጵያ ያደረገቻቸውን የልዩኑት ሃሳቦች (reservations) እና የውሳኔ ሃሳብ መግለጫዎች (declarations) ለይቶ አለማወቅ ነው፡፡ ይህን አስመልክቶ ጥናቱ እነደሚያሳው በጣም አናሳነ ለአፈፀፀም የማያስቸግሩ በተለይም ማንኛውንም አይነት የሴቶች አድልኦአዊ ልዩነት ለማስወገድ የወጣው ኮንቬንሽን አስመልክቶ ከተደረገው አንድ አንቀፅ ውጭ የሚጠቀስ ተአቅቦ እነደሌለ ነው፡፡ በመሆኑም ከዚህ ጋር በተያያዘ ፍርድ ቤቶች ስምምነቶቹን ተፈፀሚ ለማድረግ የሚያስቸግር የህግ ተግዳሮት እነደለለ በማወቅ አፈፃፀማቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡
- አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች በኢትዮጵያ የህግ እርከን ያላቸውን ቦታ ለፍርድ ቤቶች አፈፃፀም አንደ ችግር የሚጠቀስ ጉዳይ ነው፡፡ ይህን አስመለክቶ ህገ መንግስቱ አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶችን የሀገሪቱ ህግ አንደሆኑ ቢደነግግም የህግ ተዋረዳቸው ከህገ መንግስቱ ግር የሚታዩ ናቸው ወይስ እነደማንኛውም በህግ አውጭው የሚወጡ አዋጆች ጋር እኩል ይታያሉ የሚለው ጥያቄ ሲያከራክር የቆየ ጉዳይ ነው፡፡ ይህን አስመልክቶ ጥናቱ በግልፅ እነዳስቀመጠው ሚዛን የሚደፋው አመለካከት አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች ከህገ መንግሰቱ ያነሰ እርከን ቢኖራቸውም ከማንኛውም በህግ

አውጭው ከሚወጣ ህግ ግን ከፍ ያለ ቦታ አላቸው የሚለው ነው፡፡ ይህ አመለካከትም አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች በፍርድ ቤት ያላቸውን አፈፃፀም አስመልክቶ ያለውን የተበታተነ አመለካከት አቅጣጫ ያስይዛል፡፡

- አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች በፍርድ ቤቶች ያላቸው አፈፃፀም ከሃገሪቱ ካለው አጠቃላይ የሰብአዊ መብት አያያዝ፣ የህግ የበላይነትና የፍርድ ቤቶች ነፃነት፣ የባህልና የአሰራር ልምዶችና የህብረተሰቡ የሰብአዊ መብት ግንዛቤ ተለይቶ የሚታይ አይደለም፡፡ በመሆኑም በሀገሪቱ ያለውን የሰብአዊ መብቶች ግንዛቤ ማሻሻል፣ የፍርድ ቤቶችና ነፃነቶች ማረጋገጥና የህግ የበላይነትን በማህበረሰቡ ማስረፅ አስፈላጊ ነው፡፡
- ኢትዮጵያ በርካታ የሰብአዊ መብተቶችን ብታፀድቅም የተወሰኑ የሰብአዊ መብቶችን ኣላፀደቀችም፡፡ ከነዚህም የአፍሪካ የሴቶች መብት ፕሮቶኮል፣ የአለም አቀፍ የስደተኛ ሰራተኞች ኮንቬንሽንና ሰወችን በሃይል የመሰወር ድርጊትን ላመስወገድ የወጣውን ኮንቬንሽን (Convention for the Protection of All Persons from Enforced Disaapearance) ይገኙበታል፡፡ አኒዘህ የሰበአዊ መብቶችነ ማፅደቅ በሃገሪቱ ያለውን የሰብአዊ መብቶቸ ጥበቃም ይሁን ከፍርድ ቤቶች አፈፃፀም ጋር ተያይዞ ያለውን አሰራር ያጠናክራል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በአለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች የቁጥጥር ስርአት በጣም ጠቃሚ ከሚባሉትና ለሃገራዊ ሰብአዊ መብቶች ተፈጻሚነትም አይተኛ የሚባለውን የግልሰቦች በአለም አቀፍ መድረክ አቤቱታ የማቅረብ መብት (Individual Compliant Mechanism) ነው፡፡ ነግር ግን ኢትዮጵያ እነዚህ ተጨማሪ ፕሮቶኮሎች ባለማፅደቋ በዚህ ዙሪያ ሊኖር የሚችለውን አፈፀፀም ውስን ያደርገዋል፡፡